ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

## በየኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኖቭል ኮሮና ቫይረስን አስመልክቶ የተዘጋጀ ወቅታዊ መግለጫ የካቲት 01/2012

### ዓለም አቀፍ መረጃ፡

- በዓለም የጤና ድርጅት ሪፖርት መሰረት፣ እስከ የካቲት 01/2012፣  ይህ መረጃ እስከ ተጠናቀረበት ሰዓት ድረስ ያለው በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር፣  ሰላሳ ሰባት ሺህ አራት መቶ ዘጠና አራት(37494) ሲሆን፣ እስከ ዛሬ የካቲት 01/2012 ድረስ ስምንት መቶ አስራ ሶስት (813) ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ህይወታቸው አልፏል ፡፡

### ሀገር ዓቀፍ መረጃ

- በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በኖቭል ኮሮና ቫይረስ በሽታ መያዙ የተረጋገጠም ሆነ በለይቶ ማቆያ ማዕከሉ ሆኖ ክትትል የሚደረግለት ሰው የለም፣
- የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኖቭል ኮሮና ቫይረስ የላቦራቶሪ ምርመራ እዚሁ በተቋሙ ማድረግ የጀመረ በመሆኑ ወደ ደቡብ አፍሪካ ሊላክ የነበረ የ3 ሰዎች ናሙና ምርመራ በማድረግ ከቫይረሱ ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ ችሏል፡፡ በተጨማሪም የ3ቱ ወደ ደቡብ አፍሪካ ተልከው የነበሩ ናሙናዎች ውጤት የደረሰን ሲሆን ከቫይረሱ ነጻ መሆናቸዉ ተረጋግጧል፡፡
- የኖቭል ኮሮና ቫይረስን በሽታ የመከላከል ዝግጁነትን ለማጠናከር ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ እና በአዲስ አበባ ለሚገኙ 13 ሆስፒታሎች የተለያዩ ግብዓቶችን አሰራጭቷል፤ እንዲሁም ለክልል ሆሲፒታሎች ለማሰራጨት የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቀዋል፡፡
- የቫይረሱን ስርጭት አስመልክቶ እስከ አሁን ድረስ 31 ጥቆማዎች ለኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የድንገተኛ አደጋዎች  ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል (Emergency Operation Center) ደርሰው ማጣራት ተደርጎባቸዋል፣ ከነዚህ ውስጥ 14ቱ በለየታ ቆይተው ናሙናቸው ተመርምሮ ከቫይረሱ ነጻ መሆናቸው በመረጋገጡ ከለይቶ ማቆያ ማዕከሉ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡
- የበሽታውን ለየታ ስራ ለማጠናከር የለየታ ቡድኑን ለሚቀላቀሉ የጤና ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በሐዋሳ ቫይረሱን የመከላከል ዝግጁነትን ለመደገፍ ቡድን ተልኳል፡፡
- በምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን የሚመራው ብሔራዊ ግብረ ሃይል ጥር 29/2012 ስብሰባ አካሂዷል፡፡
- ለሆቴሎች፣ ታክሲ ሾፌሮች እና ለመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ዝግጅቶች ተጠናቀዋል፡፡

**ጥንቃቄ መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች**

- በተጨማሪም ሕብረተሰቡ በሀገራችን እስካአሁን በቫይረሱ መያዙ የተረጋገጠ ሰው አለመኖሩን አውቆ ሳይዘናጋ የበለጠ ጥንቃቄ ኢንዲያደርግ ኢንስቲትዩቱ ያሳስባል፡፡
- የኖቭል ኮሮና ቫይረስ ከታየባቸው ሀገራት የመጡ መንገደኞች ወይም በዚህ ቫይረስ ከተያዙ ግለሰቦች ጋር ንክኪ የነበራቸው ሰዎች ላይ የበሽታው ምልክቶች (ትኩሳት፤ ሳል፤ የትንፋሽ መቆራረጥ፣ የመተንፈስ ችግር) ከታዩ፣ ማንኛውም የሕብረተሰቡ አካል በአስቸኳይ በ8335 ነጻ የስልክ መስመር ላይ በመደወል ሪፖርት እንዲያደርግ እናሳስባለን፡፡
- የበሽታው ምልክት የታየባቸው ሰዎች በሚያስነሡጥሱበት እና በሚያስሉበት ወቅት አፍና አፍንጫቸውን በሶፍት ወይም በክንድ እንዲሸፍኑ፤ የተጠቀሙበትን ሶፍት ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ እንዲጥሉ እና እጃቸውን በውሃና ሳሙና በመታጠብ የቫይረሱን ስርጭት እንዲከላከሉ እንመክራለን፡፡

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
አዲስ አበባ
01/06/2012 ዓ.ም